# እውነት ኢ.ህአፓ አልተሸነፈምን? ደርግ-ኢ.ሠፓስ?

ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ

09-15-14

sisayraya@yahoo.com

## እንደ መንደርደሪያ

እሁድ ግንቦት 24 ቀን 2006 ዓ.ም ከስአት በኋላ በሚዩዚክ ሜይደይ ኢትዮጵያ አዘጋጅነት በብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሀፍት አጄንሲ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የአሲምባ ፍቅር በተሰኘው መጸሀፍ ላይ ያተኮረ የግማሽ ቀን ውይይ ተካሂዶ ነበር፡፡ እውነት ነው የምላችሁ ደስ የሚልና እጅግ ሲበዛ ሀሳቦችን ያፋጨና ሁለት ትውልዶችን ማለትም የቀደመውንና የአሁኑን ጎራ አስለይቶ ያከራከረ ነበር ማለትም ይቻላል፡፡ የውይይት መነሻ ሀሳቦችም በታዋቂው የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀና በደራሲ ሀይለመለኮት መዋዕል አማካኝነት የቀረቡ ሲሆን በዚህም የመጽሀፉ ታሪካዊ ዳራና ለታሪክ ተመራማሪዎች የሚኖረው ፋይዳ፣ ስነጽሁፋዊ ይዘትና የቋንቋ አጠቃቀም ቀላልነት እንዲሁም የጽሀፊው ሚዛናዊነትና የማስታወስ ብቃት በግሩም ሁኔታ ተብራርቶ ከመቅረቡም በላይ የውይይት መነሻ ሀሳብ አቅራቢዎቹ ለደራሲው አድናቆታቸውን ችረውታል፡፡

በአጠቃላይም መጽሀፉ ስሜትን ኮርኳሪና ተአማኒነት ያለው ስራ ውጤት መሆኑ ተደጋግሞ የተወሳ ሲሆን የራያዎቹ ድላይ (የደራሲው ፍቅረኛ (እውነተኛ ስሟ ስመኝ) እና ይመር ንጉሴ የደራሲውን ህይወት በማትረፍ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከተ አርሶ አደር) መጸሀፉ እንዲህ እንዲወደድና ምሉዕ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የነበራቸው ሚና ጎልቶ የወጣበት አጋጣሚ ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ በርካታ አስተያየቶች ተሰነዘሩ፣ ጥያቄዎችም ቀረቡ፣ ለተነሱ ጥያቄዎችም በአቅራቢዎቹ ምላሽ እንዲሰጥባቸው ተደረገና ውይይቱ ግለቱን ጠብቆ ቀጠለ፣ በዚህን ጊዜ ነበር የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ርዕስ ያደረግሁትን ማለትም አውነት ኢ.ህአፓ አልተሸነፈምን? የሚል ጥያቄ ከአንድ ተሳታፊ የተነሳውና ስሜት ቀስቃሽ ሀሳቦች የተለዋወጡበት፡፡

በዚህም ሀሳብ መነሻነት አንዳንድ ወጣት ተሳታፊዎች ለምን የዚያ ትውልድ ሰዎች ሽንፈታችሁን በጸጋ ተቀብላችሁ ለዚህኛው ትውልድ አዎንታዊ ትምህርት ሊሰጥ በሚችል መልኩ ሀሳባችሁንና እውነተኛ እምነታችሁን አታቀርቡም? ለራሳችሁና እናትነተው ብቻ ለተሳተፋችሁበት የትግልና የአመጽ እንቅስቀሳሴ የምትሰጡት ግምትና ለአሁኑ ትውልድ ያላችሁ አተያይ ሚዛኑን የጠበቀ ነው ብላችሁ ታምናላችሁን? እንደኔ እንደኔ በራሳችሁ ገድል ብቻ ታጥራችሁ የሌላውን ተሳትፎ ለማቀጨጭ ጥረት እያደረጋችሁ ያላችሁ ይመስለኛል የሚሉ ጥያቄ አዘል አስተያቶች ተሰነዘሩና ውይይቱ አሁንም ነፍስ ዘርቶ ቀጠለ፡፡

ይኸ ሁኔታ ነበር የእኔንም ቀልብ ስቦ እድሉን አግኝቼ በወቅቱ ሀሳቤን ለመግለጽ ባልችልም ይህችን ጽሁፍ እንዳጠናቅር ያነሳሳኝ፡፡ ምክንያቱም የመነሻ ሀሳብ አቅራቢዎቹ ራሳቸው የዚያ ትውልድ አካል ብቻ ሳይሆኑ መሪ ተዋናይም ጭምር ስለነበሩ በስሜት ውስጥ ሆነው ኢ.ህአፓ በጦር ሜዳ ቢሸነፍም ያነገበው አላማና ይዟቸው የተነሳቸው ህዝባዊ ጥያቄዎች አሁንም ድረስ አሉ፣ በዛ ላይ የኢ.ህአፓ መንፈስ እኮ አሁንም ድረስ በውስጣችን ነፍስ ዘርቶ ይላወሳል፣ እናም በአንድ ቃል በቅርቡ ቆንጂት ደበላ በፋክት መጽሄት ላይ እንደገለጸችው ኢ.ህአፓ አሁንም አልተሸነፈም ሲሉ

አስረግጠው መልስ ከመስጠታቸውም በላይ ከፊል ሽንፈትን ተቀብለው ለትምህርት የሚሆን ጠቃሚ ሀሳብም ሰነዘሩ፡፡ ልብ በሉ ኢህአፓ ከዛሬ 34 አመት በፊት ማለትም በ1972 ዓ.ም መጨረሻ ላይ በደርግና ህወሀት ጠንካራ ክንድ ተደቁሶ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረግ ውጭ የሆነ ድርጅትና ከሞላ ጎደል በሀሳብ ብቻ ያለን ፓርቲ (እስከ 1983 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአያልነሽ ይመራ የነበረው የኢህአፓ ጥቂት የታጠቀ ቡድን ጎጃም ውስጥ በጃዊ፣ በአቸፈርና በጣና በለስ አካባቢ እንዲሁም ጎንደር በቋራ አካባቢ ይንቀሳቀስ እንደነበር ሳይዘነጋ) አሁንም ድረስ አልተሸነፈም ብሎ በልበ ሙሉነት ለመከራከር መሞከር የትም እንደማያደርስ አቅራቢዎቹ በሰጡት መልስ ላይ አመላካች ሀሳብ ያቀረቡ ቢሆንም አሁንም ድረስ ሙሉ ሽንፈትን በጸጋ ተቀብሎ ለተፈጠረው ትውልድ አስጨራሽ ስህተትም በይፋ ይቅርታ የምንጠያየቅበትን ባህል መቼ ይሆን የምንለምደው? የሚል ጥያቄ እንዳነሳና እኔም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያለኝን ሀሳብ ለመሰንዘር ፈለግሁ፡፡ እግረመንገዱንም የደርግ-ኢሰፓ ሰዎች ኢህአዴግ በእድል ስልጣን ያዘ እንጂ አልተሸነፍንም ነበር እንደሚሉ ጠቆም ማድረግን ወደድሁ፡፡

## የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)ን ለምን የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ወጣቱ ትውልድ ሆ ብሎ ተከተለው?

በእኔ ግምት ኢህአፓ ይዟቸው የተነሳቸው ጥያቄዎች ማለትም መሬት ላራሹ፣ የብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች እኩልነት ይረጋገጥ፣ ህዝባዊ መንግስት አሁኑኑ ይመስረት፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበሩ፣ የዜጎች እኩል ተጠቃሚነት ይረጋገጥ፣ የኤርትራ ጉዳይ የነጻነት ጥያቄ ስለሆነ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ይሰጠው፣ በአጠቃላይም በሀገሪቱ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሰፍኖ የህግ የበላይነት ይረጋገጥ ወዘተ. የሚሉት ሀሳቦች የያኔውን ትውልድ ብቻ ሳይሆን የአሁኑንም ትውልድ ጭምር የሚያሳምኑና ለትግልም የሚያነሳሱ በመሆናቸው የሁሉንም ህብረተሰብ ክፍል በተለይም በትምህርት ላይ የነበረውን ወጣት ልብ ከማሸፈታቸውም በላይ ቀልቡን ሳቡትና ተከታዩን በእጅጉ አበዙለት፡፡

በዛ ላይ የወቅቱ ነባራዊ፣ ህሊናዊና አለምአቀፋዊ ሁኔታ ፈቅዶ የተጨቆኑ ህዝቦች ነጻነታቸውን በዘላቂነት ለመጎናጸፍ ትግል የሚያካሂዱበትና ግራዘመም አስተሳሰብ የነበራቸው አለም አቀፍ ታጋዮችና ፖለቲከኞች ጎልተው የወጡበት ዘመን የነበረ መሆኑ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ “ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቼጉቬራ” የተባለበት ወቅት መሆኑም ይህን እውነት ይበልጥ ያረጋግጣል፡፡ በአንድ ቃል ዘመኑ የትግልና የነጻነት ሀሳብ እዚህም እዚያም የሚቀነቀንበት ወቅት ስለነበር በተለይም የከተማው ትምህርት ቀመስ ወጣት ትግሉን የመቀላቀሉን ጉዳይ እንደፋሽን አድርጎ ወሰደው፣ በዚህም ምክንያት ኢህአፓ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአብዛኛው የኢትዮጵ ህዝብ ልብ ውስጥ ዘልቆ ገባ፣ ከዛም አልፎ የአፍሪካ ጥቂቱ ቮልሽቢክ (በጊዜው በነሌኒን ይመራ የነበረው የሩሲያ ቮልሽቪክ ፓርቲ እጅግ ዝነኛ ነበር) እስከመባልም ደረሰ፡፡

የደርግ አምባገነንነት ስርአትነትና ፋሽስትነትም ሳይውል ሳያድር በገሀድ ቁልጭ ብሎ ወጣና ህዝብን በአደባባይ እስከመጨፍጨፍና ወጣቱን ትውልድ በተለይ ቀይ ሽብር ይፋፋምብኝ የሚል መፈክር ደረቱ ላይ አስለጥፎ በይፋ እስከመግደል አደረሰው፡፡ ከሞላ ጎደል እነዚህና ሌሎች ወቅታዊ ሁኔታዎች ተደማምረው ኢህአፓ የኢትዮጵያን ህዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ አንቀሳቀሰ፣ የብዙዎችን ልብና ቀልብም ጭምር ማረከና በጽናት ከጎኑ ተሰልፈው የአካልና የጊዜ ብቻ ሳይሆን ክቡር የሆነውንና ምትክ የማይገኝለትን ህይወት ሳይቀር መስዋዕት እንዲያደርጉ ማሳመን ቻለ፡፡

እንግዲህ እኔ እስከ ገባኝና በእርግጠኝነት እስከማምንበትም ድረስ የኢህአፓ ገኖ መውጣት ሚስጥሩ ሌላ ነገር ሆኖ ሳይሆን ይኸውና ይኸው ሁኔታ ነበር፡፡

## የኢህአፓ ሽንፈት እንዴት ይገለጻል? እውነት ኢህአፓ አልተሸነፈምን?

የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) ያን ያህል ህዝብ ከጎኑ አሰልፎ፣ በተለይም በጠንካራ ዲስፕሊን የታነጸና የመታገል ወኔው ጣራ የነካ በአጠቃላይም ለአላማው ተፈጻሚነት መስዋዕት ለመሆን የተዘጋጀ ወጣት አቅፎና ከላይ የጠቀስናቸውን የተቀደሱ ህዝባዊ አላማዎች ይዞ ለምን ተሸነፈ? የሚለው ጥያቄ በራሳቸው በኢህአፓ መሪዎችና በታሪክ ተመራማሪዎች ተገቢ መልስ እንዲያገኝ ቢደረግ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ሊገኝበት ይችላል ብየ አምናለሁ፡፡ ለአሁኑ ውይይታችን ግን ኢህአፓ ለምንና እንዴት ተሸነፈ የሚለውን ጥያቄ ለውይይት መነሻ ይሆን ዘንድ በአጭሩ ለመመለስ እሞክራለሁና የተለየ ሀሳብ ያለው ሰው ቢኖር ሀሳቡን በማስረጃ አስደግፎ እንዲያካፍለንና አንዳች ትምህርት እንድናገኝ ያደርገን ዘንድ በዚህ አጋጣሚ እጋብዛለሁ፡፡

በእኔ የህይወት ልምድና ውስን ንባብ መሰረት ኢህአፓን ለሽንፈት ከዳረጉት ሁኔታዎች ውስጥ የመጀመሪያው የኢህአፓ ከፍተኛ አመራር በባህሪው የንዑስ ከበርቴ ወገን በመሆኑ ያን ጠንካራ የህዝብ ድጋፍ ተጠቅሞ በአቋራጭ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ ከመቋመጡ የተነሳ የደርግ ባለስጣናትን በተናጠል ጭምር በመግደልና በማስገደል የስልጣን ወንበሩን ለመቆናጠጥ ጥረት አደረገ፡፡ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞም የከተማ የትጥቅ ትግል በይፋ መጀመሩ ወቅቱን ያልጠበቀና ሚዛኑን የሳተ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በታቀደና በአግባቡ በተደራጀ የገጠር ትጥቅ ትግል አለመደገፉ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል ብዬ አምናለሁ፡፡

አሲምባን ጨምሮ በበጌምድርና በሌሎችም አካባቢዎች ሰፍሮ የነበረው የኢህአፓ ሰራዊት (ኢህአሰ) አባላት የሚገኙባቸው ቦታዎች በአብዛኛው ከተማ ላይ የተጋለጡ ወጣቶች መሰባሰቢያ ሆነው አገለገሉ እንጂ አስቀድሞ በስርአቱ ታስቦበትና ለገጠር ትጥቅ ትግሉ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት በቂ የሆነ የመሳሪያ አቅርቦትም ይሁን የስልጠና ዝግጅት ተደርጎ የተገባባቸው ነበሩ ማለትም ያስቸግራል፡፡ በዛ ላይ አመራሩ የአባሉን ሀሳብ የማያዳምጥ፣ አባሉ ለሚያነሳው ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ የማይሰጥ፣ የሀሳብ ፍጭትንም የማያበረታታ፣ ይልቁንም ለየት ያሉ ሀሳቦችና ጥያቄዎች ሲቀርቡለት አፍራሽና አንጃ ብሎ በመፈረጅ የአባላቱንና የህዝቡን መብት የሚያፍን በአጠቃላይም በሒደት ለአላማው ተገዥ መሆኑ እየቀረ ወደ አምባገነንነት እየተቀየረ መጣ፡፡

ሁለተኛው የተከተለው የትግል ስልት በተለይም የከተማው ያልተቀናጀና ከገጠር የትጥቅ ትግሉ ጋር ያልተናበበ እንዲሆን በማደርግ ረገድ የታየው መሰረታዊ ስህተት ወጣቶችን ለአደጋ ማጋለጡ ይህን ተከትሎም እነዚህን የከተማ ወጣቶች ለማዳን ሲባል ይደረግ የነበረው የእውር ድንብር እንቅስቃሴ ጊዜ ወሳጅ፣ ሀሳብ ሰራቂና ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ አልቀረም፡፡ በዛ ላይ ከሌሎች አማጽያን በተለይም ከህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ጋር የተሻለ ግንኙነት ፈጥሮ (ቢያንስ ስልታዊ የሆነ ግንባር በመፍጠር ጭምር) ትግሉን ከማቀናጀትና ውጤታማ የሚያደርግ ዘዴን ከመከተል ይልቅ ራሱን አሳብጦና የሌሎችን ሚና አሳንሶ በማየት ለኢትዮጵያ አብዮት ከእኔ በቀር ለአሳር ማለቱን አጠናክሮ ቀጠለበት፡፡

ልብ በሉ ቢያንስ የትግራይን ህዝብ ነጻ አወጣለሁ ብሎ ከተነሳውና በአብዛኛው ሲታይ ከኢህአፓ ጋር ተመሳሳይ ጥያቄ ይዞ ወደ በረሀ ከወጣው እንዲሁም ከአሲምባ በቅርብ ርቀት ላይ ይገኝ ከነበረው ህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) ጋር እንኳ መግባባት አቅጥቶት ወደ ጦርነት

ገብቶ በለኮሰው እሳት ራሱ መለብለቡ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን አሳፋሪ ስህተትም ነበር፡፡ በዚህም አንዱን ጠባብ ብሔረተኛ ሌላኛውን ደግሞ አድርባይ እያለ በመፈረጅ ወዳጅ ከማፍራት ይልቅ ጠላቶቹን እያበራከተ ሂደና በሒደት ደጋፊ አልባ እየሆነ ከመምጣቱም በላይ የራሱን የተሳሳተ የትግል ስልት በሌሎች ላይ ለመጫን ሲሞክር በደርግና ህወሀት ዱላ ክፉኛ ተቀጥቅጦ ከትግራይ መሬት ተጠራርጎ እንዲወጣ ተደረገ፡፡ ሌላኛው መሰረታዊ ጉድለቱ ደግሞ ውስጣዊ እንድነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየላላ መጥቶ መደማመጥ የማይቻልበት ሁኔታ ላይ መደረሱ ነው፡፡ የአሲምባ ፍቅር በሚለው መጽሀፍ ላይ በትክክል እንደተገለጸው የጽናት ተምሳሌ የነበሩት ግንባር ቀደም አባላቱም ጭምር ተስፋ ቆርጠው በየአቅጣጫው ተበታተኑ፣ አንዳንዶቹም "ከዚህ በኋላ ደርግን ታግሎ ማሸነፍ የራስ ጻሽን ተራራን በገመድ እንደመሳተት ይቆጠራል"፣ ስለሆነም "ከአሁን በኋላ በጥይት ቀርቶ በስፒል ተወግቶ የሚፈስ ደም የለኝም" ሲሉ በአደባባይ በገልጽ ተናግረው ትግሉን ተሰናበቱ፡፡ ከፍተኛ አመራሩም ቢሆን አባላቱ እንዲያ ግራ ተጋብተውና ተስፋ ቆርጠው ከፊሎቹ ወደ ውጭ ሲኮበልሉ ሌሎቹ ደግሞ ለደርግ መንግስት እጃቸውን ሲሰጡ ዝም ብሎ ለመመልከት ተገደደ፡፡

ታዲያ ከዚህ በላይ ሽንፈት እንዴት ሊገለጽ ይችላል? እንዳው እኛ ኢትዮጵያዊያን አመል ሆኖብን ነው መሰለኝ ከኢህአፓ ሰዎች በተጨማሪ አሁን ላይ ደግሞ አንዳንድ የደርግ ባለስልጣናት ጭምር "ደርግ እኮ አልተሸነፈም፣ ግንቦት 20ም ለኢህአዴግ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነች ትቆጠርለት" በማለት በድፍረት ሲጽፉና ሲናገሩ መስማት የተለመደ ሆኗል፡፡ የእነሱም የአልተሸነፍንም አባዜ ስርአታቸው ወደ መቃብር ከወረደ ከ23 አመት በኋላ እንኳ ክፉኛ የተጣባቸው የአስተሳሰብ በሽታ ሙሉ ለሙሉ ስላለቀቃቸው ያን ያህል ግዙፍ ሰራዊት ይዘው፣ የመንግስትን ስልጣንና ሀብት ያለተቀናቃኝ ጨብጠው በነበረበት ሁኔታ በአማጽያን ሀይሎችና በህዝብ የተባበረ ክንድ ተደቁሰው መቀመቅ መውረዳቸው ጸሀይ የሞቀውና አለም ያወቀው ሀቅ ሆኖ እያለ እንደዚያ ሁሉ በጄ ሁሉ በደጄ ሆነው በነበረበትም ወቅት ጭምር በቀላሉ የመሸነፋቸው ምስጢር ምድነው? የሚለውን ሁኔታ እንኳ አንስተው በተለይም የፖለቲካ አመራራቸውና የሰራዊቱ ድክመት የት ላይ ነበር? በማለት ጭምር ደፍረው ቢናገሩና ቢጽፉ የአሁኑ ትውልድ አንዳች ትምህርት የሚያገኝበት አጋጣሚ ይፈጠርለት ነበር ብቻ ሳይሆን እግረመንገዳቸውንም የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ሊጠይቁት በተገባም ነበር፡፡

ይባስ ብለው ኢህአዴግ በጥረቱ የተጎናጸፈውን ወታደራዊ ድል ያቃለሉ እየመሰላቸው ራሳቸውን ማታለል ይዘዋል፣ አንዳንዶቹማ ይከተሉት የነበረው የተሳሳተ የፖለቲካ መስመርና የሰራዊታቸው ዲስፕሊን መጓደል ተደማምሮ ለውድቀት ዳርጓቸው እያለም ጭምር ስለ አላማቸው ትክክለኛነት አሁንም ድረስ ለመስበክ ጥረት ከማድረጋቸው ጎን ለጎን በእነሱው አመራር ሰጭነት ለደረሰው ጥፋት ተጠያቂ ላለመሆን ሲሉ ኢህአፓን ጨምሮ የሌሎችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ህጸጽ በማጉላት ራሳቸውን ከደሙ ንጹህ ለማድረግ ይውተረተራሉ (በዚህ ረገድ በቅርቡ እኛና አብዮቱ የሚል ርዕስ ሰጥተው በማሳተም ገበያ ላይ ያዋሉትን የሻምበል ፍቅረስላሴ መጽሀፍን ይመለከቷል)፡፡ ለመሆኑ መቼ ይሆን ከዚህ አይነት የመታበይና ቀቢጸ ተስፋ የወረሰው አዙሪት አስተሳሰብ ወጥተን በግልጽ የምንነጋገረውና ለተፈጸመው ታሪካዊ ስህተትም ይቅርታ የምንጠያየቀው?

በፍትህ አደባባይ ሳይቀር ጨፍጫፊነታቸው በማስረጃ ተረጋግጦ የረዥም አመታት ጽኑ እስራትና ሞት ጭምር የተፈረደባቸው የደርግ ባለስልጣናትም ሆኑ የአፍሪካው ጥቁር ቦልሸቪክ ተብሎ እስከመሰየም ደርሶ የነበረው የኢህአፓ መሪዎች አባላቱን እንዲያ ሜዳ ላይ በትነው የቀይ ሽብር ሰለባ በማድረግ "ምሳ ሊያደርጉን ያሰቡንን ቁርስ አደረግናቸው" ሲያስብሉ ቆይተው ሁለቱም ወገኖች አሁንም ድረስ አልተሸነፍንም ብለው ሲከራከሩ መስማታችንስ ተገቢ ነውን? እርግጥ ነው

ኢ.ህአፓ ያነሳቸው ጥያቄዎች በቀድሞው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢ.ህዴን) በአሁኑ ብአዴን /ኢ.ህአፓ ውስጥ ሲታገሉ የነበሩና ኢ.ህአፓ መፈራረሱ እርግጠኛ መሆኑን አስቀድመው የተገነዘቡ የበለሳው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (የእርማት እንቅስቃሴ) አባላት የመሩት ቡድን አሁንም ቢሆን መታገል ይቻላል ብለው ህወሀት ይቆጣጠረው ወደ ነበረውና ተክራርዋ በመባል ወደ ሚታወቀው የትግራይ መሬት በመሄድ 35 ወንዶችና 2 ሴቶች በድምሩ 37 ወጣቶች በመሆን የመሰረቱት የፖለቲካ ድርጅት ነው/ እና በህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) አማካኝነት ከግንቦት 20/1983 ዓ.ም ጀምሮ ምላሽ እንዲያገኙ ጥረት እየተደረገ ነው በማለት የሚከራከሩ ወገኞች አሉና ለእነዚህስ ሰዎች መልሳቸው ምን ይሆን? እንግዲህ ሰው ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም ነውና ነገሩ እኔ ይህን ለማለት ሞክሬያለሁና እስቲ በጉዳዩ ላይ እንወያይበት፡፡